በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁ፡-201990

ቀን፡-01/02/2014ዓ.ም

ዳኞች ፡- ብርሀኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሀኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች ፡- ማክሼብ ኃ/የተ/የግ/ማህበር - አልቀረቡም

ተጠሪ ፡- ወጋገን ባንክ አክሲዮን ማህበር- አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ የብድር ውል ይፍረስልኝ በሚል የቀረበ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ጉዳዩ በተጀመረበት የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

አመልካች ታህሳስ 18 ቀን 2012 ዓ.ም በተፃፈ ክስ ከተጠሪ ጋር ሚያዝያ 11 ቀን 2011 ዓ.ም በተደረገ የብድር ውል ስምምነት ብር 2,631,246.08 መበደሩን፣ አከፋፈሉም ውሉ ከተደረገበት ጊዜ ጀምሮ በየሶስት ወሩ ሁኖ ወለድና የተለያዩ ወጪዎችን ጨምሮ ብር 349,124.00 መሆኑንና በ8 ጊዜ ክፍያ በ2 ዓመት ውስጥ እስከ ሚያዝያ 11 ቀን 2013 ዓ.ም ተከፍሎ እንዲጠናቀቅ መስማማታቸውን ነግር ግን ተጠሪ ክፍያው በ7 ጊዜ እንዲጠናቀቅ ማድረጉን፣ ይህም የሒሳብ መዝገብ አያያዝ ላይ ችግር መፍጠሩን፣ የወለድ መጠኑ ላይም ከፍተኛ ልዩነት በማምጣት የተስተካከለ የኦዲት ሪፖርት እንዳይኖር እክል መፍጠሩን፣

በዚህም ምክንያት አመልካች የ2012 ዓ.ም የግብር ክሊራንስ አግኝቶ የንግድ ፍቃዱን ለማሳደስ አለመቻሉን እና ተጠሪም ይህን ለማስተካከል ፍቃደኛ አለመሆኑን ጠቅሶ የብድር ውሉ እንዲፈርስ ዳኝነት ጠይቋል፡፡

ተጠሪ የካቲት 24 ቀን 2012 ዓ.ም በተፃፈ መልስ የብድር ስምምነቱ የተደረገው አመልካች ከመሰቦ ሲሚንቶ ፋብሪካ ጋር ባደረገው የማሽነሪ አቅርቦት ውል መሰረት ግዴታውን ባለመወጣቱ ተጠሪ በሰጠው መጠኑ ብር 2,631,246.08 የሆነ የቅድመ ክፍያ እና የመልካም ስራ አፈፃፀም ዋስትና መሰረት ለመሰቦ ሲሚንቶ ፋብሪካ ሰኔ 28 ቀን 2010 ዓ.ም ክፍያ በመፈፀሙና ይህ የአመልካች እዳ ወደ ብድር ውል እንዲዞር በመስማማታችን ነው፡፡ እዳው በ2 ዓመት ጊዜ ውስጥ በየ3 ወሩ በ8 ጊዜ ተከፍሎ የሚያልቅ ሲሆን በዚህ ላይ ምንም አይነት ልዩነት አልተደረገም፡፡ በውሉ በተገለጸው እና በታሰበው ሒሳብ ላይ ልዩነት የመጣው ተጠሪ እዳውን ለመሰቦ ሲምንቶ ፋብሪካ ከከፈለበት ጊዜ አንስቶ የብድር ውሉ እስከተደረገበት ሚያዝያ 10 ቀን 2011 ዓ.ም ድረስ የታሰበ ወለድ ነው፡፡ በመሆኑም ውሉ ሊፈርስ አይገባም በማለት ተከራክሯል፡፡

ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ ተጠሪ ክፍያውን በ7 ጊዜ እንዳጠናቅቅ አስገድዶኛል በሚል አመልካች ለውሉ መፍረስ በምክንያትነት የጠቀሰው ከውሉ ጋር በቀጥታ የሚገናኝ አይደለም፡፡ ውሉን ተከትሎ ባለ አፈፃፀም ተጠሪ በፃፈው ደብዳቤ ላይ የተፈጠረ እክል በመሆኑ ደብዳቤው እንዲሰረዝ ወይም በውሉ መሰረት እንዲፈፀም አመልካች መጠየቅ እየቻለ በፍ/ሕ/ቁ 1784 እና 1785 መሰረት አይነተኛ የውል መጣስ በሌለበት ውሉ እንዲፈርስ መጠየቁ ተገቢ አይደለም በማለት ክሱን ውድቅ አድርጎታል፡፡

አመልካች ውሳኔውን በመቃወም ለፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ ቅሬታውን ያቀረበ ሲሆን በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሰረት በመሰረዙ ጥር 28 ቀን 2013 ዓ.ም የተፃፈ ሰበር አቤቱታውን አቅርቧል፡፡

የአቤቱታው ይዘት ባጭሩ በስር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር ብድሩ በ2 ዓመት ጊዜ ውስጥ በየ3 ወሩ ለ8 ጊዜ ተከፍሎ እንዲያልቅ ስምምነት የተደረገበት መሆኑን ነገር ግን በአፈፃፀም ሒደት በ7 ጊዜ እንዲከፈል መደረጉን ተጠሪ ባልካደበት የፍ/ሕ/ቁጥር 1784 እና 1785 ድንጋጌዎች እንደማያሟላ ተደርጎ የውል ይፍረስልኝ ጥያቄው ውድቅ መደረጉ ተገቢ አይደለም፡፡ ውሉ ሊፈርስ አይገባም ቢባል እንኳ በአማራጭ በተጠየቀው ዳኝነት መሰረት ቀሪውን የብድር እዳ በሚመለከት አመልካች እና ተጠሪ መጀመሪያ በተደረገው ስምምነት መሰረት ውላቸውን ሊያሻሽሉ ይገባል ተብሎ መወሰን ነበረበት፡፡ እንዲሁም በግራ ቀኙ የተጠቀሱ ምስክሮች ሳይሰሙ መወሰኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የሰበር አቤቱታው በአጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ የአመልካችን የዳኝነት ጥያቄ የስር ፍ/ቤት ውድቅ ያደረገበትን አግባብ ግራ ቀኙ ሚያዝያ 11 ቀን 2011 ዓ.ም ካደረጉት የገንዘብ ብድር ውል አንቀፅ 2 እና ከፍ/ሕ/ቁጥር 1784ና 1785 ጋር በማገናዘብ ለመመርምር ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪ መልሱን እንዲያቀርብ ትዕዛዝ ተሰጥቷል፡፡

ተጠሪ መጋቢት 15 ቀን 2013 ዓ.ም የተፃፈ መልስ ያቀረበ ሲሆን በግራ ቀኙ መካከል በተደረገው የብድር ውል ስምምነት አንቀፅ 2.1. በተገለፀው የአከፋፈል ሁኔታ ክፍያው በ8 ጊዜ እንዲጠናቀቅ ከተደረገው ስምምነት በተቃራኒ ተጠሪ በ7 ጊዜ ተከፍሎ እንዲጠናቀቅ አለማድረጌን በስር ፍ/ቤት በግልፅ ክርክር አቅርቤአለሁ። አመልካችም ክፍያው ከ8 ዙር ወደ 7 ዙር ስለመቀየሩ ምንም አይነት ማስረጃ ያላቀረበ ሲሆን የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ በሰነድ ማስረጃ የሚረጋገጥ በመሆኑ የሰው ምስክር ሳይሰማ ክሱ ውድቅ መደረጉ ተገቢ ነው በማለት ተከራክሯል።

አመልካች ሰኔ 9 ቀን 2013 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልሱን ያቀረበ ሲሆን የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር ተከራክሯል።

የክርክሩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም በግራ ቀኙ መካከል ሚያዝያ 11 ቀን 2011 ዓ.ም የተደረገው የብድር ውል ሊፈርስ አይገባም ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት በስር ፍ/ቤት ከተደረጉ ክርክሮችና ከተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች እንዲሁም ለጉዳዩ ተገቢነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረነዋል።

እንደመረመርነው በግራ ቀኙ መካከል ሚያዝያ 11 ቀን 2011 ዓ.ም በተደረገ የብድር ውል ስምምነት አመልካች ብር 2,631,246.08 መበደሩን፣ አከፋፈሉም ውሉ ከተደረገበት ጊዜ ጀምሮ በየሶስት ወሩ ሁኖ ወለድና የተለያዩ ወጪዎችን ጨምሮ ብር 349,124.00 መሆኑንና በ8 ጊዜ ክፍያ በ2 ዓመት ውስጥ እስከ ሚያዝያ 11 ቀን 2013 ዓ.ም ተከፍሎ የሚጠናቀቅ መሆኑ ግራ ቀኙን አላከራከረም። አመልካች ከዚህ ስምምነት በተቃራኒ በአፈጻም ሒደት ተጠሪው ክፍያው በ7 ጊዜ እንዲፈፅም አድርጓል፤ ይህንንም ክዶ አልተከራከረም በሚል ያቀረበውን ቅሬታ ስንመለከት አመልካች ድርጊቱን አለመፈፀሙን በግልጽ ክዶ ስለመከራከሩ በስር ፍ/ቤት ፍርድ ላይ ሰፍሯል። ተጠሪ ይህንን ፍሬ ነገር ማለትም የክፍያው ጊዜ ወደ ሰባት ዙር መቀየሩን ክዶ እስከተከራከረ ድረስ አመልካች ክፍያው ከ8 ዙር ወደ 7 ዙር መቀየሩን የሚያሳይ ማስረጃ በማቅረብ በፍ/ህ/ቁጥር 2001/1 እና በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁጥር 223 ክርክሩን በማስረጃ ሊያረጋግጥ ይገባል። ይሁን እንጂ አመልካች ተጠሪ ክዶ አልተከራከረም ከሚል በስተቀር ይህንን ፍሬ ነገር ለማስረዳት ማስረጃ ስለማቅረቡ ወይም አቅርቦ አላግባብ ውድቅ የተደረገበት ስለመሆኑ ያቀረበው ክርክር የለም። በመሆኑም ተጠሪ የክፍያ ጊዜ ለውጥ አለማድረጉን ክዶ የተከራከረ እና በአመልካች በኩል የክፍያ ጊዜ ለውጥ በተጠሪ ለመደረጉ የቀረበ ማስረጃ በሌለበት ተጠሪ በአመልካች ለውል ማፍረሻ ተደርጎ የቀረበውን የክፍያ ጊዜ ለውጥ አድርጓል ለማለት አይቻልም።

ሌላው ከዚህ ጋር ተያይዞ መታየት ያለበት አመልካች ከውል ስምምነቱ ውጪ ተጠሪ ክፍያው በ7 ጊዜ ተከፍሎ እንዲጠናቀቅ ቢጠይቅ እንኳ ውሉን ለማፍረስ በቂ ምክንያት ይሆናል? ወይስ አይሆንም? የሚለው ይሆናል። ከተዋዋዮቹ አንዱ እንደ ውሉ ያልፈፀመ እንደሆነ ሌላኛው ተዋዋይ እንደ ውሉ እንዲፈፀምለት ወይም ውሉ እንዲሰረዝ እና ለደረሰበት ጉዳት ካሳ መጠየቅ የሚችል መሆኑ በፍ/ሕ/ቁጥር 1771 ላይ ተገልጿል። ውል እንዲረዝ ሲጠየቅ ዳኞች ጥያቄውን ተቀብለው ውሉ እንዲሰረዝ የሚወስኑት በውል

ግዴታው በተገለፀው አግባብ በሙሉ ወይም በከፊል ባለመፈፀሙ ብቻ ሳይሆን በውሉ ላይ አይነተኛ የውል መጣስ ሲከሰት (Fundamental breach of contract) እና የውሉ መሰረዝ ለተዋዋዮቹ ጥቅምና ለቅን ልቦና አስፈላጊ ሁኖ ሲገኝ ስለመሆኑ በፍ/ሕ/ቁጥር 1784 እና 1785 ላይ ተመላክቷል፡፡ አመልካች ውሉ እንዲሰረዝ በምክንያትነት የሚያነሳው ተጠሪው አከፋፈሉን በሚመለከት ከብድር ስምምነቱ በተቃራኒ በ7 ጊዜ ውስጥ እንድከፍል አድርጎኛል ይህም በሒሳብ አያያዝ እና በንግድ ፈቃድ እድሳት ላይ እክል ፈጥሮብኛል በማለት ነው፡፡ ተጠሪው ክፍያው በ7 ጊዜ እንዲጠናቀቅ ቢያደርግ እንኳ ይህ ድርጊት አመልካች በውሉ ከተገለፀው ጠቅላላ የብድር መጠን በላይ እንዲከፍል በማድረግ መሰረታዊ የውል መጣስን የሚያስከትል አይደለም፡፡ በተጨማሪም አመልካች ውሉን መሰረት አድርጎ በውሉ በተገለፀው አግባብ ክፍያውን በ8 ዙር ከፍሎ ከማጠናቀቅ የሚከለክለው ነገር ስለሌለ የሂሳብ አያያዙን በዚህ አግባብ በማስተካከል የንግድ ፍቃድ እድሳቱን ማስተካከል የሚችል ሲሆን የሂሳብ አያያዙም ሆነ የንግድ ፍቃድ እድሳቱ ለውሉ መሰረታዊ ጉዳይ አይደለም፡፡ ይህም የግራ ቀኙን ጥቅም የማያስጠብቅ ለቅን ልቦናም ተቃራኒ በመሆኑ አመልካች ውሉ እንዲሰረዝ የጠየቀው ዳኝነት የፍ/ሕ/ቁጥር 1784 እና 1785 ድንጋጌዎች መመዘኛን አያሟልም ተብሎ መወሰኑ ተገቢ ነው፡፡

በመቀጠልም አመልካች በአማራጭ በተጠየኩት ዳኝነት ቀሪውን የብድር እዳ በሚመለከት መጀመሪያ በተደረገው ስምምነት መሰረት ውላችንን እንድናሻሽል አለመወሰኑ ተገቢ አይደለም በማለት የሚያነሳውን መከራከሪያ ስንመለከት የስር ፍ/ቤት የክርክር ሒደት አመልካች ይህን የአማራጭ ዳኝነት ስለመጠየቁ አያመላክትም፡፡ በተጨማሪም ፍርድ ቤቶች በውል መሰረት እንዲፈጸም ወይም ውሎች እንዲፈርሱ ወይም እንዲሰረዙ ወይም በውሎቹ መሰረዝ ወይም ዘግይቶ በመፈም ምክንያት የደረሰ ጉዳት ካለ ካሳ እንዲከፈል ከሚያደርጉ በቀር የህጉን መመዘኛ አሟልቶ የተደረገ ውል እንዲሻሻል ውሳኔ የሚያስተላልፉበት የሕግ አግባብ የለም፡፡

በመጨረሻም አመልካች በጉዳዩ የሰው ምስክር አለመሰማቱን ጠቅሶ የሚከራከር ቢሆንም በፍትሐብሔር ክርክር ማስረጃ የሚሰማው እና ፍሬ ነገሩ በማስረጃ እንዲነጥር የሚደረገው የግድ አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ብቻ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ በአመልካች በኩል ውሉ እንዲፈርስ ለማስወሰን የተጠቀሰውን ምክንያት ውሉን ለማፍረስ በቂ ምክንያት ነው ወይስ አይደለም የሚለውን በራሱ ከሕጉ ጋር በማገናዘብ ድምዳሜ ላይ መድረስ የሚቻል በመሆኑ በጉዳዩ ላይ የሰው ምስክር መስማቱ የግድ አስፈላጊ አይደለም፡፡ በመሆኑም አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረበው ቅሬታ ተገቢነት የለውም፡፡

ሲጠቃለል አመልካች ከተጠሪ ጋር ያደረገው የብድር ውል እንዲፈርስ ያቀረበው ምክንያት ተጠሪ የብድሩ መክፍያ ጊዜ ከ8 ወደ 7 ዙር ተቀይሯል በሚል ሲሆን ይህንን ተጠሪ ስለማድረጉ በማስረጃ የተረጋገጠ አለመሆኑ የአመልካችን የውል ይፍረስልኝ ክርክር ውድቅ ለማድረግ በቂ ከመሆኑም በላይ የተጠቀሰው የውል ማፍረሻ ምክንያት በህጉ አነጋገር አይነተኛ የውል መጣስ በተጠሪ ተፈጽሟል የሚያስብል አይደለም፡፡

በመሆኑም በስር ፍ/ቤቶች ውሉ ሊፈርስ አይገባም መባሉ ህጉን የተከተለ ነው ከሚባል በስተቀር የተፈጸመ መሰረታዊ ሕግ ስህተት የለም በማለት ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በፍ/መ/ቁጥር 242750 ህዳር 30 ቀን 2013 ዓ.ም እንዲሁም የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በይ/መ/ቁጥር 201347 ጥር 27 ቀን 2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሠጠው ትዕዛዝ በፍ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት የተደረገው ክርክር ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

ሄ/መ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡